OVERLAKE MEDICAL CENTER

OVERLAKE MEDICAL CLINICS

የጤና አገልግሎት አቅራቢዮት የሆነውን ኦቨርሊክ የጤና ማእከልን ስለመረጡ እናመሰግናለን፡፡ በተቻለው መጠን ለግልጋሎቱ ከመዘገቡበት ግዜ አንስቶ የህክምናዎት ሂሳብ እስኪዘጋ ድረስ ቆይታዎት መልካም እንዲሆን እንፈልጋለን፡፡ ከጤና ግልጋሎቱ ጋር ተያይዞ የገንዘብ ችግር ሊኖር እንደሚችል እንገነዘባለን ለዚህም ሊያግዙት የሚችል እቅድ አዘጋጅተናል፡፡ በእቅዱ ላይ የሚሮቶትን ማንኛውንም አይነት ጥያቄና ለርሶ የሚስማማዎትን እቅድ መምረጥ እንዲችሉ የገንዘብ ጉዳይ አማካሪ እናቀርብሎታለን፡፡

## የቅናሽ ክፍያ እቅድን ማስተዋወቅ

እንሂሁም ታካሚው ለመድህን ዋስትና ብቁ ሆኖ ነገር ግን የጥቅማጥቅሙ ጣራ ላይ በመድረሱ የመድህን ሽፋኑን የማያገኝ ከሆነ እቅዱ ተግባሪዊ ይሆናል፡፡ እንዲሁም ታካሚው ለመድህን ዋስትና ብቁ ሆኖ ነገር ግን የጥቅማጥቅሙ ጣራ ላይ በመድረሱ የመድህን ሽፋኑን የማያገኝ ከሆነ እቅዱ ተግባሪዊ ይሆናል፡፡ ታካሚው ለኦቨርሌክ የጤና ማእከል ከሚከፍለው ሙሉ ክፍያ ላይ እና/ወይም ኦቨርሌክ የጤና ማእከል በ 30 ቀናት ውስጥ የመጀመሪያውን ክፍያ ከከፈለ የ 30% ቅናሽ ያገኛል፡፡ ቅናሹን የሚያገኙበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ለገንዘብ ጉዳይ አማካሪውን በ 425.688.5655 ወይም 425.688.5299 በመደወል ማግኘት ይችላሉ፡፡

## የተራዘመ የክፍያ እቅድ

ከወለድ ነፃ የሆነ የክፍያ እቅድ እንዲያገኙ አብረኖት በመስራታችን ደስተኞች ነን፡፡ ትክክለኛው ወርሀዊ ክፍያዎትን የኮንትራቱ እርዝማኔ በሂሳቦት ሁኔታ የሚወሰን ይሆናል፡፡ ሁሉም የወርሀዊ ክፍያ እቅዶች የሚወሰኑት የኦቨርሌክ የገንዘብ ጉዳይ አማካሪ በሚያወጣው የኮንትራት እቅድና መጠን መሰረት ነው፡፡ የክፍያ እቅዱን በተመለከተ ጥያቄ ካሎት፣ እባክዎትን በ 425.688.5299 ይደውሉ፡፡

## የገንዘብ ድጋፍ እቅድ

የመድህን ዋስትናው ክፍያውን ከተፈለ በኋላ ወይም የመድህን ሽፋን ጥቅማጥቅም ከሌለ የሚጠየቀውን የገንዘብ ድጋፍ ይህ እቅድ ያቀርባል፡፡ በአገልግሎቱ ግዜ በሚኖር የገንዘብ ሁኔታን የሚወሰን ሆኖ ከሂሳቦት ላይ 65% እስከ 100% የሚሆን ቅናስ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ ቅናሹ በገቢዎት ፐርሰንቴጅ መጠን የፌደራል የድህነት መመሪያ ከሂሳቦት ጋር በመሆን የሚወሰን ነው፡፡ ይህንን እቅድ ለመተግበር አገልግሎቱን ካገኙ በኋላ እና/ወይም የገንዘብ ሀላፊነት እንዳለቦት ባቁበት ቅፅበት የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ መጠየቅና መሙላት ይኖርቦታል፡፡ ማመልከቻው ስለገቢዎት የሚጠይቅ ሲሆን ማመልከቻው በሚታይ ግዜ ኦቨርሌክ ሆስፒታል ማህበር የጤና ዱቤ (የዱቤ መጠኖት ላይ ተፅእኖ እንደሌለው) የማግኘት መብት ያሎት እንሆን እሱን ያረጋግጣል፡፡ ስለዚህ እቅድ ዝርዝር ማብራሪያ ወይም ማመልከቻ ለመጠየቅ በ 425.688.5299 ይደውሉ፡፡ የገንዘብ ድጋፉ የሚገኘው ሌሎቹ የክፍያ አማራጮችን ዳሽን የሶስተኛ-ወገን የእዳ ጉዳዮችን በሙሉ ከተቀበሉ (ለምሳሌ - የመኪና ወይም ሌላ የአደጋ ሽፋን) በኋላ ነው፡፡